የሠ/መ/ቁጥር 198669
ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ወንድማገኝ ታደሰ- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አጋር የጥበቃ አገለግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በሐረር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ ለጥበቃ ስራ ከቀን 01/02/2010 ዓ/ም ጀምሮ በወር ብር 1,293.00 ደመወዝ እየከፈለ ሊያሰራቸዉ ቀጥሯቸዉ እስከ ቀን 13/02/2011 ዓ/ም ድረስ እየሰሩ ቆይተዉ በስራ መመዝገቢያ ላይ ፊርሜ የተረከብኩት ጥበቃ ቀጠና ውጪ ሌላ ቀጠና ላይ ሂደህ የጥበቃ ሥራ እንዲሰሩ ሲያዛቸዉ በሥራ መመዝገቢያ ላይ ፊርሜ የተረከብኩት ጥበቃ ቀጠና ላይ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ እሆናለሁ በማለታቸዉ ብቻ በቀን 13/02/2011 ዓ/ም ከሥራ እንዳሰናበታቸዉ ገልጸዉ ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 22,487.08 ተጠሪ እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ተጠሪ የአመልካችን መብት ሳይነካ በተመሳሳይ ቦታ ላይ ተዛውረዉ እንዲሰሩ አዘዛቸዉ እንጂ ተጠሪ አመልካችን አላሰናበታቸዉም፡፡ተጠሪ በተዛወሩበት ቦታ እንዲሰሩ በጽሁፍ ቢታዘዙም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ተጠሪ የዓመት እረፍት ተጠቅመዋል፡፡ስለሆነም እንዲከፈላቸዉ

የጠየቁት ክፍያዎች አይገባቸዉም፡፡የሸምዝና የጫማ በሚል እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት 6000.00 ብር ያለአግባብ የጠየቁትና የተጋነነ ስለሆነ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 50384 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 03/07/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የተመደብኩበትን ቦታ ትቼ ወደሌላ ምድብ ብሄድ ፈርሜ በተመደብኩበት ቦታ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ ስለምሆን በሌላ ምድብ አልሰራም በማለቱ አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የአመልካች የሥራ ዉል ከሕግ-ወጭ ተቋርጧል ሲል ወስኗል፡፡ይህንን ተከትሎም የአገልግሎት ክፍያ የ2 ዓመት ብር 1,724.00፣ የካሳ ክፍያ ብር 1,293.00 ፤ የሥራ ውሉ በተጠሪ አነሳሽነት ከሕግ-ዉጭ ስለተቋረጠ በአንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ ካሳ ብር 1,293.00 ፣ በአንቀጽ 43 መሰረት ከሕግ-ውጪ የስራ ዉሉ በመቋረጡ የአመልካች የቀን ደመወዝ በ180 ተባዝቶ ካሳ ብር 7,758.00 ፣ የ28 ቀን የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ብር 1,206.60፣ ክፍያ ለዘገየበት ብር 3,879.00 ፤ የጥበቃ ደንብ ልብስና ጫማ በአመት 2 ጊዜ የ2010 እና 2011 ዓ/ም በግራ ቀኙ ያልተካደ ቢሆንም የዋጋ ዝርዝር በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ በአማካይ ብር 3,000 እንዲሁም ወጪ ኪሳራ በቁርጥ 500 ብር አጠቃላይ ብር 19,360.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 20027 ላይ በቀን 30/10/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ አቤቱታውን ለሀረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ችሎቱ በመ/ቁጥር 00101 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/02/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለሥራ ውሉ መቋረጥ መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በቀን 13//02/2011 ዓ/ም  በተመደቡበት የሥራ ቦታ በሥራ ሰዓት ባለመገኘተቻዉ በቦታቸው ሌላ ሠራተኛ ተመድቦ አመልካች አርፍደዉ በመምጣቱ ተጠሪ አመልካችን በሌላ ቦታ ጥበቃ ቀጠና በዚያው በተቀጠረው ቅጥር ግቢ ምንም አይነት የደመወዝ ቅነሳ ሳያደርግ በያዘው ደመወዝ መብትና ጥቅም ጋር ያዛወረውን አመልካች ባለመቀበላቸዉ እንደሆነ ከክርክሩ መረዳት ችለናል፡፡ተጠሪ የአመልካችን ለሥራው አመቺ በሆነ ቦታ አዘውሮ ማሰራቱ አስተዳደራዊ ስልጣኑ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች በኩል ቅን ልቦና አለመኖሩን ለመረዳት ችለናል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የጉዳዩን አመጣጥና የተጠሪን የአስተዳደር ስልጣን ግምት ውስጥ ሳያስገባ እና አመልካችን ከስራ አላሰናበትትኩም አሁን ተመልሶ መስራት ይችላል የሚል ክርክር አቅርቦ እያለ ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የሥራ ውል አቋርጧል በማለት የሠጠዉ ዉሳኔ አበዋጅ ቁጥር 1156/2011 ከአንቀጽ 23 እስከ 45 የተደነገገዉን ያላገናዘበ በመሆኑ አግባብ አይደለም በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 03/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የሥር

መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የሥራ ዉል የተቋረጠዉ በተጠሪ ጥፋት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ተጠሪ ምንም ዓይነት የዝውውር ደብዳቤ ሳይሰጠኝ እና ሳይደርሰኝ በሌላ ቀጠና ሄጄ እንድሰራ ሲያዘኝ አስቀድሞ ፈርሜ የተረከብኩት ንብረት ቢጠፋ ተጠያቂ ስለሚሆን የፈረምኩት ፊርማ እንዲሰረዝልኝ በማለቴ ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ያለማስረጃ ያቀረበዉን ክርክር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበሉና የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ መሻሩ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የሰበር ችሎት አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ከመሆኑ አኳያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሶስት ዳኞች ተሰይመዉ የወሰኑበትን አግባብ ሰበር አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ከመሆኑ አኳያ የሀረር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሶስት ዳኞች ብቻ ጉዳዩን አይቶ የወሰነበት አግባብ እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 26/11/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የሚከተለው ነው፡፡

ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበተው አመልካች እንደሚሉት ሳይሆን አመልካች ሥራ ከገቡ በኋላ የተመደቡበትን ሥራ ቦታ ላይ እየሰራ እያለ ሌላ ክፍተት ያለበት ቦታ ላይ ሄደዉ እንዲሰሩ ሲመደቡ አልሄደም ከዚህ ከተመደብኩበት ቦታ ውጪ አልሰራም በማለታቸዉ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ሌላ ቦታ ላይ የመደበዉ አመልካችን ተጠያቂ ለማድረግ ሳይሆን የሥራ ክፍተትን ለመሸፈን ነው፡፡በተጨማሪም በኃላፊው ታዞ በሌላ ስራ ላይ የተመደበ ሰራተኛ ተጠያቂ የሚሆነው ለተመደበበት ቦታ እንጂ በኃላፊው ታዞ ለተነሳበት ቦታ አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ የሀረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ በተጨማሪ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ለማየት የቻለበትን የሕግ መሰረት መርምረናል፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የክልል ጉዳይ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ላይ እና በሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 70(2/ሐ) ላይ እንደተመለከተዉ ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነዉ መሰረት የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለዉ ተደንግጓል፡፡ይህንን ተከትሎ በወጣዉ ሕግ በሐረሪ ሕዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል በወጡ አዋጆችና እንደገና ለማሻሻል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 68/1999 አንቀጽ 7(ሀ እና ለ) (ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 107/2004 እንደገና

ቢሻሻልም ይህ አንቀጽ አልተለወጠም) ስር ከተደነገገዉ መረዳት የሚቻለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚኖሩት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ሦስት ዳኞች (አንድ ሰብሳቢ ዳኛና በሁለት ተጨማሪ ዳኞች) ተሰይመዉ እንደሚዳኙ ደንግጓል፡፡በሌላ በኩል በቀድሞዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988(በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 10/4 እና ይህንን አዋጅ ከነማሻሻያዉ በሻረዉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/2 ላይ በተደነገገዉ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስችለዉ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት እንደሆነ የተደነገገ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነዉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ እንጂ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ አይደለም፡፡ይህም ታሳቢ ያደረገዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የየክልላቸዉን ሕገ መንግስትና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ የሚሰየሙትን ዳኞች ብዛት የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸዉ ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 185278 ላይ በቀን 25/01/2013 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ላይ እና በሌሎች መዝገቦች ላይ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት ዉሳኔ በመስጠቱ የተፈጸመ ስህተት እንደሌለ ተገልጾ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱም ሕገ መንግስታት በተፈቀደዉ መሰረት ባወጣዉ ሕግ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሦስት ዳኞች እንደሚያስችል በተደነገገዉ መሰረት ይህንን ጉዳይ ሦስት ዳኞች ተሰይመዉ በሰበር አይተዉ በመወሰናቸዉ ከአሰያየም አንጻር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ የተያዘዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ የሥራ ዉል ማቋረጫ ምክንያት ነዉ ተብሎ በሕግ የተደነገገ በቂ ምክንያት ሳይኖር ተጠሪ አመልካችን የሥራ ዉል ማቋረጡን ማረጋገጡን ገልጾ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ላይ እነደተመለከተዉ ተጠሪ እንደ አሠሪ ሠራተኛዉን ሥራ ወዳለበት አዛዉሮ የማሰራት መብት ያለዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጠዉ መልስ ያቀረበዉ ክርክር አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል እንጂ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ የሚል አይደለም፡፡አመልካች ደግሞ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማስረጃ ተጠሪ እንዴት በሕገ-ወጥ መንገድ እንዳሰናበታቸዉ አስረድተዉ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ በሕግ ከተመለከተዉ አግባብ ዉጭ ተጠሪ አመልካችን እንዳሰናበታቸዉ የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ አረጋግጦ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በሐረሪ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 70(2/ሐ) ላይ እንደተደነገገዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተወሰነ የክልል ጉዳይ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የሚገኝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ከማረም ባለፈ ማስረጃ መዝኖ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር አረጋግጦ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ ዉሳኔ እንዲሰጥ ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ከሕግ ዉጭ አላሰናበተም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ዉሳኔ የሻረዉ ማስረጃ በመመዘን ጭምር በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ካለ በኋላ የወሰናቸዉ ክፍያዎችን እንደመረመርነዉ አመልካች ክሱን ያቀረቡት ተጠሪ ከሕግ-ዉጭ ከሥራ አሰናብቶኛል በሚል ሆኖ እያለና በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32/1 ስር በተመለከቱ ምክንያቶች የሥራ ዉሉ እንደተቋረጠ ባልተረጋገጠበት የሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል የሠጠዉ ዉሳኔ የሕግ መሰረት ስለሌለዉ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡እንዲሁም የጥበቃ ደንብ ልብስና ጫማ በአመት 2 ጊዜ የ2010 እና 2011 ዓ/ም አልተሰጠኝም በሚል አምላከች ብር 6000.00 እንዲከፈላቸዉ ጠይቀዉ የሥር ፍርድ ቤት በርትዕ 3000.00 እንዲከፈላቸዉ የወሰነዉም ቢሆን የደንብ ልብስ የሚሰጠዉ በሥራ ላይ ተገኝቶ ለሚሰራ ሠራተኛ በመሆኑ የሥራ ዉሉ ሲቋረጥ አብሮ የሚቋረጥ እንጂ ሕገ-ወጥ ስንብት በተፈጸመ ጊዜ አሠሪዉ ወደ ገንዘብ ለዉጦ እንዲከፈል የሚገደድበት ጥቅማጥቅም ባለመሆኑ ከዚህም አንጻር የተሠጠዉ ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ የሚከተለዉን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00101 ላይ በቀን 26/02/2013ዓ/ም የሠጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የሐረሪ ክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 50384 ላይ በቀን 03/07/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20027 ላይ በቀን 30/10/2012ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሻለዋል፡፡

3. የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል እና የደንብ ልብስና የጫማ በሚል በርትዕ ብር 3000.00 እንዲከፍል የወሰነዉ ብቻ ተሽሮ ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እ ንጂ ለፍርድ አፈጻጸ ምዓለ ማእያገለግልም